# በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተንጠልጥሎ…

ከሃብሮማይ
Ghabrom@yahoo.com

የአገራችን ሁኔታ ስንቃኝ፣ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ማየትና ነገ መሆን ያለበትን ደግሞ ካለው ነባራዊ ሁኔታ በማየት መተንበይ የግድ ይላል፡፡ አንድ ነገር ይሆናል ወይም አይሆንም የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አሁን ካለበት ተጨባጥ ሁኔታ መነሳት ይኖርብናል፡፡ አሁን ያለውን ሳንገነዘብ፣ሳናስተውልና ሳንመዝን ሰለ ነገ ማሰብ በጭፍን እንደመጓዝ ነው፡፡

ስለመጪው ምርጫ 2002 ስናስብ ካለፈው የ 97ቱ ምርጫ ትምህርት ተወስዶ፣ በዛን ጊዜ የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በማጤን፣ ጠንካራውን በበለጠ እንዲጎለብት በማድረግ፣ ደካማውን ደግሞ እንዳይደገም አሽቀንጥሮ በመጣል፣ መጪውን ምርጫ ከማንም ጊዜ በተሻለ ሰላማዊ ፣ፍትሃዊ፣ታማኝና ነፃ እንዲሆን ጥረት መደረግ እንዳለበት እሙን ነው፡፡

ምርጫውን ነጻ፣ሰላማዊና ፍትሃዊ ብሎም ታማኝ ለማድረግ፣ በሕገ መንግስቱ መሰረት ከማንም ያልወገነና ነጻ የሆነ የምርጫ ቦርድ ተቋቁሟል፡፡ የምርጫ ቦርድ አባላት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት ነጻ ናቸው፡፡ የ 2002 የምርጫ ቦርድ በ 1997 ምርጫ ከተቋቋመው የምርጫ ቦርድ ለየት የሚያደርገው፣ በሕገ መንግስቱ መሰረት የምርጫ ቦርዱ አባላት የመጠቆም ስልጣን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠ ቢሆንም፣ ሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች ነፃ ናቸው የሚሏቸውን ግለሰቦች እንዲጠቁሙ መደረጉና የጠቆሟቸው ግለሰቦችም በቦርዱ አባላት ውስጥ መካተታቸው ነው፡፡ ይህ እርምጃ የተወሰደው መጪው 2002 ምርጫ ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ ፍትሃዊ፣ነፃ፣ግልፅና ታማኝነት ያለው ምርጫ ለማድረግ መንግስት ካለው ቁርጠኝነት የመነጨ ይመስለኛል፡፡ መንግስት ምርጫውን የተሻለ ለማድረግ ግማሽ መንገድ ተጉዞ ሌሎች ፓርቲዎች ምርጫውን ሰላማዊ እንዲሆን ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው እያሳየ ነው፡፡ ይህ በመንግስት በኩል ያየነው መልካም ጅምር ነው፡፡

በተጨማሪም ገዢው ፓርቲም ምርጫውን ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ተአማኒነት ያለው እንዲሆን በፓርቲው ጋባዥነት በምርጫ ስነምግባር ደምብ ዙርያ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ድርድር እያካሄደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይህን ፓርቲው መጪው ምርጫ ከምን ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ፍትሃዊና ታማኝ እንዲሆን እያደረገው ያለውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ መቀጠል አለበት እላለሁ፡፡ ይህ በስነምግባር ደምብ ዙርያ የሚደረግ ውይይት በዋናኛነት ፓርቲዎቹ በምርጫ ወቅት ሲንቀሳቀሱ ሊከተሉት በሚገባቸው ነጥቦች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ውይይቱ አገራችን የጀመረችውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡

መጪው ምርጫ ፍትሃዊና ሰላማዊ እንዲሆን፣ ምርጫ ቦርዱና ገዢው ፓርቲ ብቻ መንቀሳቀሳቸው በቂ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎቻችም መጪው ምርጫ በሁሉም መለኪያ ነፃ፣ፍትሃዊና ታማኝ ለማድረግ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ በምርጫ 97 የነበረውን ሁከትና ብጥብጥ እንዳይደገም ያለፉ ስህተቶቻቸውን አርመው፣ የህዝባችን ሉዓላዊነት በሚገለጽበት ምርጫ ላይ፣ አገራዊ አጀንዳ ይዘው በጨዋታው ሕግ ብቻ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ተገንዝበው መዘጋጀት እንደሚጠበቅባቸው አያጠያይቅም፡፡

የስምንት ፓርቲዎችና የሁለት ግለሰዎች ስብስብ የሆነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ "መድረክ" የአገሪቷ የዴሞክራሲ ሒደት አጋር መሆን ሲገባቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች ለህዝብና ለአገር የማይጠቅም ስራዎች ሲተገብሩ ይስተዋላሉ፡፡

መድረክ ለሰላማዊ ትግሉ ዝግጁ የሆነ ፓርቲ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም በመድረክ ስም እንቅስቃሴ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የሚያከናውናቸው የነበሩ ስራዎች ሳሰታወሰው የተለያዩ ፀረ ዴሞክራሲ የሆኑ ተግባሮችን በማከናወን ላይ እንደነበር ማሰታወስ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ያህል የኔዘርላንድ ኤምባሲ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በመጋበዝ ሊያወያያቸው ሲል የመድረክ አመራሮች "ኢዴፓ" ከተባለ ፓርቲ ጋር አንወያይም ካልሆነ በዚህ ስብሰባ ላይ አንሳተፍም በማለት ኢዴፓን ለማግለል መሞከራቸው ይታወሳል፡፡ ይህ ደግሞ በመቻቻል ላይ የተመሰረተ ውይይት ብሎም ድርድር እንደማይቀበሉ አቋማቸውን በግልፅ ያሳዩበት አጋጣሚ ነው፡፡ ማንኛውን ፓርቲ ህጋዊ በሆነ መንገድ ሃሳቡ የመግለፅ መብት እንዳለው እሙን ነው፡፡ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት በሕገ መንግስቱ በማያሻማ መልኩ የተቀመጠም ነው፡፡ ሃሳብን የመግለጽ መብት ከዴሞክራሲያዊ መብቶች በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መድረክ ይህን ሃሳብን በነፃ የመንሸራሸር መብት ያስፈራዋል መሰለኝ ከላይ ከጠቀስኩት ፓርቲ ጋር አልወያይም ብለዋል፡፡ ሃሳብን በነፃ እንዳይሸራሸር እንቅፋት የሚሆን ፓርቲ ፀረ ዴሞክራሲ ፓርቲ ነው፡፡ መድረክም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡

በሌላም እንደሚታወቀው ዴሞክራሲያዊ አሰራር የሚከተሉ አገሮች ምርጫን ያካሂዳሉ፡፡ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ነፃና በህዝብ ተአማኒነት ያለው ለማድረግም በምርጫ ዙርያ የተለያዩ መመሪያዎች መኖራቸው አይቀርም፡፡ ከነዚህ መመሪያዎች አንዱና ምናልባትም ዋነኛው የስነ ምግባር መመሪያ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው በስነምግባር ደንብና መመሪያ የማይገዙ ከሆነ ብሄር ከብሄር፣ ጎሳ ከጎሳ፣ ነገድ ከነገድ፣ ጎጥ ከጎጥ ወዘተ የሚያጋጭ አደገኛ ፕሮፓጋንዳ በመጠቀም ህዝቡ ወዳልተፈለገ ሁከትና ብጥብጥ በማስገባት ተጀምሮ ያለውን ልማት የሚያደናቅፍና የአገሪቱን ሰላም የሚያውክ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በመሆኑም መጪው ምርጫ ሰላማዊ ለማድረግ ከየፈለገ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በስነ ምግባር ደንብ ዙርያ ተወያይተው ልዩነታቸውን አቻችለው መጪው ምርጫ ሰላማዊ ለማድረግ ቆርጠው መነሳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሰሞኑን በስነምግባር መመሪያ ዙሪያ በገዥው ፓርቲ ጋባዥነት በፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገው ውይይት ደግሞ የዚህ መገለጫ በመሆኑ በውይይቱ ላይ የተካፈሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ዓላማቸው መጪው ምርጫ ፍትሃዊ፣ ሰላማዊ፣ ነፃና ታማኝ እንዲሆን ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በመሆኑ፡፡

ይሁን እንጂ መድረክ የተባለ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ የተቀደሰ ዓላማ ያለው የስነ ምግባር ውይይት ለመካፈል ዝግጁ ስላልነበረ የተለያዩ ቅደመ ሁኔታዎችን በመደርደር ራሱን ከሌሎች ፓርቲዎች በላይ በመቁጠር ስብሰባውን ረግጦ መውጣቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ለምንድነው መድረክ በስነምግባር መመሪያ ዙርያ መወያየትና መደራደር ያልፈለገው? የሚል ጥያቄ መመለስ ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ የስነ ምግባር መመሪያው እውን ከሆነ መጪው የ 2002 ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ነፃና ታማኝ እንደሚሆን ስለሚያውቁ ይህ ደግሞ ህውከትና ነውጥ ፈላጊ ለሆነ ድርጅት የሚመች ባለመሆኑ ይመስለኛል፡፡ መድረክ መጪው ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ ብሎም ታማኝ እንዳይሆን የተደበቀ ፍላጎት ያለው ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳ መድረክ ስብሰባውን ረግጦ ቢወጣ ከስህተቱ ተፀፅቶ ሊመለስ ቢፈልግ መሳተፍ እንደሚችል ዕድል መሰጠቱ ለአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ ሊመሰገን የሚገባ ነገር ነው፡፡

ሰሞኑን ደግሞ መድረክ ጉባዔ አካሂዶ ነበር፡፡ በጉባዔው አመራሮችን መምረጡም ሰምተናል፡፡ ለመጪው አራት ወራት መድረክን በፕሬዝዳንትነት እንዲመሩ የተመረጡት ዶክተር መራራ ጉዲና ናቸው፡፡ ከላይ እንደገለፅኩት መድረክ ያደርጋቸው የነበሩ እንቅስቃሴዎች አብዛኛዎቹ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ባህሪይ የተላበሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስትና ሀዝብ በንቃት ሊከታተለው ሊጠነቀቅ ይገባል እላለሁ፡፡ ዶክተር መራራን በፕሬዝዴንትንት ለምን መረጧቸው? ብሎ መጠየቁ ተገቢነት ያለው ይመስለኛል፡፡ ዶክተሩ እንደ ማንኛውም ዜጋ የመምረጥና የመመረጥ ሕገ መንግስታዊ መብት እንዳላቸው ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ዶክተር መራራ ያለፈውን ድርጊታቸውና አሁን ያሉበትን አካሄድ ስገመግም ብስለት ያለው፣ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ተፋቅረውና ተከባብረው እንዲኖሩ የሚያደርግና በልዩነታችን ላይ አንድነትን የሚሰብኩ ሰው እንዳልሆኑ ለሁላችን የሚያስማማ ይመስለኛል፡፡ ሰውየው የፖለቲካል ሳይንስ ምሁርና ረጅም ተመክሮ ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን አንደበተ ርቱዕና የአገሪቷ የዴሞክራሲ ሒደት አጋር መሆን ሲጠበቅባቸውና ለዜጎች ጥሩ አርአያ በመሆን የሕገመንግስቱ ተገዢ መሆን ሲገባቸው በተቃራኒ በተንኳሽ ድርጊታቸውና

በተሳዳቢነታቸው የሚታወቁ መሆናቸው ሳስበው የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈራም ጭምር ነው፡፡

ዶክተሩ ስለመጪው ምርጫ ለአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ጳጉሜ 3/ 2001ዓ/ም በሰጡት አስተያየት ሃገሪቱ ሰላም እንድትሆን ከተፈለገ እንደ ዝምባብዌና ኬንያ የስልጣን መጋራት ከተደረገ ብቻ መሆኑ ነግረውናል፡፡ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ስልጣን የሚገኘው ህዝቡ በሚሰጠው ድምፅ ብቻ ነው፡፡ይሁን እንጂ እንደ ዶክተር መራራ አነጋገር ህዝብ በካርዱ የሚሰጠውን ውጤት ለመቀበል ዝግጁነት እንደሌላቸው በገሃድ ተናግረዋል፡፡ የሰውየው ፍላጎት ሕገ መንግስቱን በመናድ ስልጣንን መጋራት እንደሆነ በማያሻማ መልኩ ነግረውናል፡፡ ይህ የሚያሳየን ደግሞ ሰውየው መጪው ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊ፣ ታማኝና ነፃ እንዳይሆን በሎም በአገራችን ሁከትና ብጥብጥ እንዲነሳ ከወዲሁ መዘጋጀታቸው ነው የሚያሳየን፡፡

በተጨማሪም እንደሚታወቀው ዋና ፅሕፈት ቤቱ ብራስለስ የሆነ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ (ICG) ካለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ርእዮተዓለማዊ አስተሳሰቡ በመነሳት መጪው የ 2002 ምርጫ ሰላማዊ ሊሆን እንደማይችልና ብጥብጥና ሁከት መነሳቱ እንደማይቀር መዘገቡ ይታወሳል፡፡ ይህ መሰረት የለሽ ሪፖርት የአገሪቷ ምስል ለማበላሸትና የተያየዘችውን ሰላም፣ ዴሞክራሲና ቀጣይነት ያለውን ልማት ሆን ተብሎ ጥላሸት ለመቀባት የታለመ ሪፖርት መሆኑን ኢትዮጵያ ያለችውን ተጨባጭ ሁኔታ በንፁህ አእምሮው ላየ፣ የ አይ ሲ ጂ ሪፖርት መሰረተ የለሽ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይችላል ብዬ እገምታለሁ፡፡

ዶክተር መራራ ጉዲና ከአንድነት ድምፅ ሬድዮ ባደረጉት ቃለ ምልልስ አይ ሲ ጂ ያቀረበውን ተራ ሪፖርት ሲያደንቁ ተደምጠዋል፡፡ እኔም ከዚያ የተለየ ግምገማ የለኝም ሲሉም ሰምተናል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሰውየው መጪው ምርጫ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ሰላማዊ ብሎም ታማኝ በማድረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አጋር ሆነው ለመስራት የተዘጋጁ ሳይሆን እንደ የ አይ ሲ ጂ ሪፖርት ብሎም የዶክተር መራራ ግብ ምርጫውን ሰላማዊ እንዳይሆን ጥረት ማድረግና በአገሪቷ ሁከትና

ብጥብጥ እንዲኖር እየተነበዩ መሆናቸው ከዚህ በላይ ማረጋገጫ ያለ አይመስለኝም፡፡

እንግዲህ ዶክተሩ በመጪው 2002 ምርጫ የስልጣን መጋራት ካልተደረገ በሌላ አነጋገር ሕገ መንግስቱ ካልተናደ የሁከትና ብጥብጥ መድረክ እንደሚሆን ነው የደስኮሩልን፡፡ የመድረክ ፓርቲ ከላይ እነደገለፅኩት ከመጀመርያ ጀምሮ የሚደርጋቸው የነበረና ያለ ተግባራት ፀረ ዴሞክራሲ መሆናቸውና ይህንን ሊያሳኩለት ዘንድ በፕሬዝዳንትነት የመረጣቸውን ሰውየም ዶክተር መራራ መሆናቸው መጪውን ምርጫ የተሳካ እንዳይሆን ካላቸው ፈላጎት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም የመድረክ ባህሪይ ላይ የዶክተር መራራ አመራርነት ሲጨመረው በእሳት ላይ ቤንዚን ነውና! አበው ሲተርቱ "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተንጠልጥሎ…" እንዳሉት የመድረክን አካሄድ መንግስትና ህዝብ በጥንቃቄ ሊያዩት ይገባል እላላሁ፡፡

በመሆኑም የመድረክ ሰዎች ካለፈው ምርጫ'97 አካሄድ የተማሩ አይመስሉም፡፡ በተገኘው ሰፊ የፖለቲካ ምህዳር መንቀሳቀስ ሲገባቸው ልክ በምርጫ '97 እንደተሞከረ ሁሉ ሕገ መንግስታዊውን ስርአት በመናድ በነውጥና በሁከት ስልጣን ካልተቆጣጠርን ብለው በአሁኑ ፕሬዝዳንትነታቸው ነግረውናል፡፡ ምክንያቱም ሰውየው ሲመርጡት ካለው አቋም በመነሳት ነውና፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ለማንም እንደማይጠቅም ህዝቡን በሚገባ አውቋልና ባለው የፖለቲካ ምህዳር ተጠቅመው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ቢንቀሳቀሱ ይሻላል እላለሁ፡፡ ሰላም!